# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ

# የትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ምልመላና ምደባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር --/2017 (ረቂቅ)

መጋቢት/2017 ዓ.ም
ትምህርት ቢሮ

**መግቢያ፤**

ትምህርት ኮሌጆች የትምህርትና ስልጠና፣ የጥናትና ምርምር እና የማሕበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲወጡ ብቁና ተነሳሽነት ያላቸውን ዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ግልጽና አሳታፊ የሆነ የውድድር መስፈርቶችን በመጠቀም በውድድር መምረጥና ማሰማራት በተቋማቱ አጠቃላይ አፈፃፀም ላይ የላቀና ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ከዚህ መነሻ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን ተከትሎ የመጡ ለውጦችን መምራት የሚችሉ፤ መልካም ስብዕና የተላበሱ፣ ብቃት እና ተነሳሽነት ያላቸውን ዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ከክልሉ አከባቢዎች ግልፀኝነትንና ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልኩ በማወዳደር መምረጥና ስምሪት መስጠት በማስፈለጉ፤

የትምህርት ኮሌጆችን ለማስተዳደር በርዕሰ መስተዳድር ምክር ቤት የወጣ ደንብን ተከትሎ የትምህርት ኮሌጆች ዲንና ምክትል ዲኖች ተግባርና ኃላፊነት ግልጽና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የትምህርት ኮሌጆች አቅም በማሳደግ የልህቀት ማዕከል እንዲሆኑ መስራት በማስፈለጉ፤

የክልሉን የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ችግሮችን በጥናትና ምርምር በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ በማመላከት ለትምህርት ጥራትና ተገቢነት አስተዋጽኦ የሚያበረክት ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ በመስተዳድር ምክር ቤት የትምህርት ኮሌጆችን ለማስተዳደር በወጣ ደንብ ቁጥር 38/2017 በአንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ ሰ) ላይ በተሰጠ ስልጣንና ኃላፊነት የትምህርት ኮሌጆች ዲንና ምክትል ዲኖች ምልመላና ምደባ ሥርዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ፤**

ይህ መመሪያ "የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ምልመላና ምደባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር ---/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ፤**

2.1) "ክልል" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ነዉ፤

2.2) "ቢሮ" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው፤

2.3) "ደንብ" ማለት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የትምህርት ኮሌጆችን ለማስተዳደር በመስተዳድር ምክር ቤት የወጣ ደንብ ቁጥር 38/2017 ነው፤

2.4) "የትምህርት ኮሌጅ" ማለት የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ መምህራን፣ የትምህርት አመራር እና የትምህርት ባለሙያዎች የሚሰለጥኑበት የትምህርት ኮሌጅ ነው፡፡

2.5) "የስራ አመራር ቦርድ" ማለት በደንብ ቁጥር 38/2017 አንቀጽ 14 መሰረት በቢሮ የሚሰየምና ትምህርት ኮሌጆችን በበላይነት የሚያስተዳድር የእያንዳንዱ የመንግስት ትምህርት ኮሌጅ የስራ አመራር ቦርድ ነው፤

2.6) "ዋና ዲን" ማለት የትምህርት ኮሌጅን ለማስተዳደር በምልመላና መረጣ ሂደት ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ የተመደበ የትምህርት ኮሌጁ የበላይ ኃላፊ ነው፤

2.7) "ምክትል ዲኖች" ማለት የትምህርት ኮሌጅን ለማስተዳደር በምልመላና መረጣ ሂደት ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ የተመደቡ የአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲኖች ወይም የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲኖች ነው፤

2.8) "አወዳዳሪ ኮሚቴ" ማለት የትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንና ምክትል ዲኖችን ለማወዳደር የተዋቀረ አካል ነው፤

2.9) "መምረጫ መስፈርት" ማለት ለትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንነት ወይም ምክትል ዲንነት የሚያበቃ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ እና በመመሪያ ላይ የተመላከቱ ተጨማሪ መስፈርቶችን በመጠቀም ተወዳዳሪዎችን በውጤታቸው ለመለየት የተቀመጠ መለኪያ ነው፤

2.10) "ሜሪት" ማለት በአመልካቾች መካከል ልዩነት ሳይደረግ በእውቀት፣ በክህሎት እና በችሎታ ላይ የተመሰረተ የምልመላና ምደባ ሥርዓት ነው፤

**አንቀጽ 3 የአወዳዳሪ ኮሚቴ ተጠሪነት፤**

አወዳዳሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለትምህርት ኮሌጆች ለሥራ አመራር ቦርድ ነው፤

**አንቀጽ 4 አወዳዳሪ ኮሚቴ ማቋቋም፤**

ከዚህ በኃላ "አወዳዳሪ ኮሚቴ" ተብሎ የሚጠራው የትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንና ምክትል ዲኖችን በማወዳደርና የውድድር ሂደቱን በመምራት በውድድሩ ከ1 እስከ 5 ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን በቅደምተከተል በመመዝገብ ለሥራ አመራር ቦርድ የሚያቀርብ አካል ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት በትምህርት ቢሮ የሚቋቋም ነው፤

**አንቀጽ 5 ስለ አወዳዳሪ ኮሚቴ አሰራር ነፃነት፤**

አወዳዳሪ ኮሚቴ በኃላፊነት፣ ሚስጥርን በመጠበቅ፣ በቅንነት፣ በነፃነትና ከጥቅም ግጭት፣ ከማንኛውም አካል ከኃይማኖት እና ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በፀዳ መልኩ ሥራውን የማከናወን ነፃነት ይኖረዋል፤

**አንቀጽ 6 የተፈጻሚነት ወሰን፤**

ይህ መመሪያ በክልል ትምህርት ቢሮ ስር በሚገኙ በማንኛውም የመንግስት ትምህርት ኮሌጆች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 7 የጾታ አገላለጽ፤**

በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸዉ ለሴት ጾታ ያገለግላል፤

**አንቀጽ 8 ዓላማ፤**

በዚህ መመሪያ የሚተገበረው የትምህርት ኮሌጆች ዲንና ምክትል ዲኖች ምልመላና ምደባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፤

8.1) ለትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ከክልሉ አከባቢዎች ግልፀኝነትንና ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልኩ ብቁና ተወዳዳሪ እጩዎችን መምረጥ እና መመደብ፤

8.2) የክልሉን የትምህርት ጥራት ችግሮችን በጥናትና ምርምር በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ማመላከት የሚችል ለትምህርት ጥራትና ተገቢነት አስተዋጽኦ የሚያበረክት ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖር ማድረግ፤

8.3) የትምህርት ኮሌጅ ዲንኖችና ምክትል ዲኖች እጩዎችን የማወዳደርና የመምረጥ ሥርዓትና ሂደቱ ኮሌጁን የልህቀት ማዕከል ሆኖ እንዲወጣ የሚያስችል ስትራቴጅክ አመራር ማምጣት ነው።

## ክፍል ሁለት

## የአወዳዳሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት፤

### አንቀጽ 9 የመልማይ ኮሚቴ አባላት ብዛት፤

የትምህርት ኮሌጆች የዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ውድድር፣ ምልመላና ልየታ የሚያከናውኑ አካላት ከተለያዩ ተቋማት የሚመረጡ ሆኖ በግል ስብዕናና ሥነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ፤ የአካዳሚክ ብቃትና ሥራ ልምዳቸውን ታሳቢ ያደረገ 5 (አምስት) አባላት ያሉት አወዳዳሪ ኮሚቴ ይደራጃል፤

### አንቀጽ 10 የትምህርት ኮሌጆች ዲንና ምክትል ዲኖች አወዳዳሪ ኮሚቴ አባላት፤

10.1) ከትምህርት ኮሌጆች ከሥራ አመራር ቦርድ አባላት መካከል የሚሰየም የአወዳዳሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤ (1)

10.2) ከክልል ትምህርት ቢሮ ከመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም ከፍተኛ ባለሙያ የመልማይ ኮሚቴ ፀሐፊ፤ (1)

10.3) ከትምህርት ኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን አባላት መካከል በአባላቱ ስምምነት ወይም በምርጫ የሚሰየም አባል፤ (1)

10.4) ከትምህርት ኮሌጁ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አባል፤ (1)

10.5) የትምህርት ኮሌጁ ከሚገኝበት አከባቢ ውጪ በክልሉ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔ ከሰኔት አባላት የሚወከል አባል፤ (1)

### አንቀጽ 11 አወዳዳሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፤

የትምህርት ኮሌጆች በፍትሐዊነት፣ በብቃትና በውድድር በሚመረጡ ግለሰቦች እንዲመሩ አወዳዳሪ ኮሚቴ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይወጣል፤

11.1) ዝርዝር ተግባራትንና ለሥራው የሚያስፈልገውን በጀት የያዘ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባል፤ ስፀድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

11.2) አወዳዳሪ ኮሚቴ የሚያከናውናቸውን ውይይቶች፣ ስብሰባዎች፣ ውሳኔዎች፣ ቃለ-ጉባኤዎችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች መረጃ በሰነድነት አደራጅቶ በከፍተኛ ጥንቃቄና በሚስጥር ይይዛል፤

11.3) በቂ ተወዳዳሪዎች እንዲያመለክቱ ግልፅ ማስታወቂያ ያወጣል፤

11.4) ቅጂ የትምህርት ማስረጃውን ከዋና የትምህርት ማስረጃ ጋር የተመሳከረ ማስረጃ በመያዝ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ምዝገባ ያካሂዳል፤ የተመዝጋቢዎችን መረጃ ያደራጃል፤

11.5) የስልጠና ሰርትፍኬቶች ከትምህርት አመራር ወይም ከጥናትና ምርምር ወይም የዕቅድ አዘገጃጀት ወይም የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወይም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ወይም የተከታታይ ምዘና ወይም ሰልጣኝ ተኮር ስነ-ዘዴ፤ ጭብጦች ዙሪያ ስለመሆኑ አረጋግጦ ይመዘግባል፤

11.6) ዝቅተኛ መስፈርት አሟልተው የተመዘገቡ ተወዳዳሪዎች መረጃ በማደራጀት ለቀጣይ ውድድር ሂደት ብቁ የሆኑትን በመለየትና በመፈራረም ለሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባል፤

11.7) መመልመያ መስፈርቱን አሟልተው ለፕሮፖዛል ገለፃ ውድድር የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን በመፈራረም በማስታወቂያ ይገልፃል፤ ለሥራ አመራር ቦርድ ያሳውቃል፤

11.8) በውድድር ሂደቱ ቅሬታ ቢኖር አንኳን ሂደቱን ለማረም ይቻል ዘንድ የፕሮፖዛል ገለፃ፣ ጥያቄና ምላሹ በተንቀሳቃሽ ቪዲዮ ተቀርፆ ለመረጃነት እንዲያገለግል ያደርጋል፤

11.9) በካችመንት ከሚነገሩ ቋንቋዎች መካከል ቢያንስ አንዱን መፃፍ፣ ማንበብ፣ መናገርና መስማት መቻል ግዴታ በመሆኑ አመልካቹ ከዞን ወይም ልዩ ወረዳ ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረቡን ያረጋግጣል፤

## ክፍል ሶስት

## የትምህርት ኮሌጆች የዲንና ምክትል ዲኖች የወድድር ሂደትና ምደባ፤

**አንቀጽ 12 አመልካቾችን በማስታወቂያ ለውድድር ስለመጋበዝ፤**

የትምህርት ኮሌጆች የዋና ዲን፣ የአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲን እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያዎች በክልሉ ትምህርት ቢሮ ዌብ-ሳይት ወይም በትምህርት ኮሌጆች ዌብ-ሳይት ወይም በተቋሙ አከባቢ በሚገኝ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን መለጠፍ ወይም መውጣት አለባቸው፤

**አንቀጽ 13 ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ የሚያካትታቸው መሠረታዊ ጉዳዮች፤**

13.1) የተቋሙ ስምና አድራሻ፤

13.2) ክፍት የሥራ መደብ መጠሪያ፤

13.3) ደረጃና ደመወዝ፤ የተመደቡ ጥቅማጥቅሞች ካሉ፤

13.4) ክፍት የሥራ መደቡ ብዛትና የመደብ መታወቂያ ቁጥር፤

13.5) የሥራ መደቡ የሚጠይቀው የትምህርት ዓይነት፣ ደረጃ እና ልምድ፤

13.6) የሥራ መደቡ የሚፈልገውን መሠረታዊና ቴክኒካዊ የብቃት ልክ፤ የዕውቀት፣ የክህሎት፣ የአመለካከት እና ሌሎችም ተፈላጊ ችሎታዎች፤

13.7) ለምዝገባ መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎችና ማመልከቻዎች፤

13.8) ምዝገባ የሚጀምርበትና የሚጠናቀቅበት ቀንና ሰዓት፤

13.9) የምዝገባ ቦታና የቢሮ ቁጥር፤ መያዝ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 14 ማስታወቂያው ክፍት ሆኖ በአየር ላይ የሚቆይበት ጊዜ፤**

14.1) የትምህርት ኮሌጆች ዋና ዲንና ምክትል ዲኖች የሥራ መደቦች ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ማስታወቂያው ክፍት ሆኖ ይቆያል፤

14.2) የአመልካቾች ምዝገባ የሚጀምረው ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ሆኖ በአንቀጽ 14) ንዑስ አንቀጽ 14.1. ላይ በተጠቀሰው ተከታታይ የሥራ ቀናት ይካሄዳል፤

14.3) አመልካቾች በግንባር ወይም በሕጋዊ ተወካዮቻቸው አማካይነት ቀርቦ መመዝገብ ይችላሉ፤

**አንቀጽ 15 ስትራቴጅክ ዕቅድ ገለፃና ቃለ መጠይቅ ወቅት የሚታደሙ አካላት፤**

ተወዳዳሪዎች የቃለ መጠይቅና የስትራቴጂክ እቅድ ገለጻ ሲያደርጉ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተወከሉ የሰኔት አባላት፣ የትምህርት ኮሌጁ የሥራ ማኔጅመንት

አባላት፣ የትምህርት ኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን አባላት እና የትምህርት ኮሌጁ ማህበረሰብ ተወካዮች በቦታው በመገኘት ሂደቱን ይከታተላሉ፤

**አንቀጽ 16 ስትራቴጅክ ዕቅድ ገለፃና ቃለ መጠይቅ የሚቀርብበት ቋንቋ፤**

የትምህርት ኮሌጁ የስልጠና ቋንቋ፣ የሚያደርጋቸው አለም አቀፍ ግንኙነቶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ በመሆኑ ተወዳዳሪዎች የስትራቴጅክ ዕቅድ ገለፃ እና የቃለ መጠይቅ ምላሹን የሚያደርጉት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይሆናል፤

**አንቀጽ 17 የትምህርት ኮሌጆች የዋና ዲንና ምክትል ዲኖች ውጤት አሰጣጥ፤**

ለትምህርት ኮሌጆች ለዋና ዲንነትና ምክትል ዲንነት ክፍት የሥራ መደቦች ለሚወዳደሩ ዕጩዎች ሥራ ላይ የሚውሉ የመምረጫ መስፈርቶችና የሚኖራቸው ዋጋ በዚህ መመሪያ በጥቅል እና ተቀጽላ በተደረገው ንዑሳን የማወዳደሪያ መስፈርቶች የተቀመጠ በመሆኑ በመመሪያው የተያያዘውን የማወዳደሪያ ንዑሳን ነጥቦች ተቀጽላዎችን እንደ መነሻ በመጠቀም አወዳዳሪ ኮሚቴው እያንዳንዱን ጥቅል ተዛማጅነት በሚኖራቸው ርዕሶችና ለውድድር አመቺ በሆነ መንገድና በማያሻማ ሁኔታ መሸንሸኑን በማረጋገጥ በኮሚቴ አባላት የተሰጠ ነጥብ አማካይ ይወሰዳል፤

17.1) **የትምህርት ደረጃና ዝግጅት** (15%)

ለዋና ዲን ወይም ለአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲን ወይም ለአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ክፍት የሥራ መደቦች ላይ የሚወዳደሩ እጩዎች የትምህርት ደረጃ ሁለተኛ ድግሪና በላይ ሆኖ በትምህርት ዕቅድና አስተዳደር ወይም በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጥናት ወይም በትምህርት ምርምር ወይም በሥርዓተ ትምህርት ጥናት ወይም በስነ-ትምህርት ወይም በፔዳጎጂ ወይም በትምህርት ኮሌጆች በሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ዝግጅት ያሏቸው እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

17.2) **የሥራ ልምድ** (15%)

ተወዳዳሪዎች ከትምህርትና መሰል ተልዕኮ ካሏቸው ተቋማት በትምህርት አመራርነትና በከፍተኛ ባለሙያነት፤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር፣ በምርምር ሥራ እና በማህበረሰብ አገልግሎት ስለማገልገላቸውና ጉልህ አስተዋጽኦ ስለማበርከታቸው በሚቀርቡ መረጃዎች ይረጋገጣል፤

17.3) **የጥናትና ምርምር ስራዎች** (5%)

በትምህርት ኮሌጆች ለዋና ዲን ወይም ለአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲን ወይም ለአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ክፍት

የሥራ መደቦች ላይ የሚያመለክቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ጉዳዮች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በአለም አቀፍ ወይም በሀገር አቀፍ እውቅና ባላቸው ጆርናሎች ላይ መታተማቸው ይረጋገጣል፤

17.4) **መልካም ስነ ምግባር** (5%)

ተወዳዳሪዎች በሰሩባቸው ተቋማት በተባባሪነታቸውና በመልካም ስነ ምግባር ማገልገላቸው ከተቋማት ውድድሩ ከሚካሄድበት የቅርብ ጊዜ ወይም በሶስት ወራት ውስጥ በቀረበ ማስረጃ ይረጋገጣል፤

17.5) **የስልጠና ሰርተፍኬቶች** (5%)

ተወዳዳሪዎች በሥራ ላይ ቆይታቸው ያከናወኑት ተግባራትና ሌሎቹም ተያያዥነት ያላቸው የስልጠና ሰርተፍኬቶች እንደ ውድድር መስፈርት ታሳቢ ይደረጋሉ።

17.6) **የስትራቴጂክ ዕቅድ ይዘት፤ ችግር ፈቺነትና ወቅታዊነት** (25%)

ለውድድር የሚቀርብ ስትራቴጂክ ዕቅድ የትምህርት ኮሌጁን ተልዕኮዎች፣ የክልሉን የትምህርት ጥራት፣ ተገቢነትን ሊያረጋግጥ የሚችል፤ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ በሚደረገው ርብርብ በትምህርት ዘርፍ በዕውቀት፣ በክህሎትና በሥነ ምግባር የታነጸ እንዲሁም በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የላቀ የሰው ሀይል ለማፍራት ስለሚከተሉት ስልት፣ የእቅዱ ችግር ፈቺነትና ወቅታዊነት፣ የትምህርት ኮሌጁን የልህቀት ማዕከል ለማድረግ ስለሚከተሉት አመራርና ተጨማሪ ሃብት ለማግኘት የነደፉት ስልት፣ የተቋሙን አስተዳደር ለማሻሻል የሚያደርጉት ጥረትና የተቀመጠበት አግባብ፣ ከሌሎች አቻና ተዛማጅ ከሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ጉድኝቶችን ለመፍጠር ያስቀመጧቸው ስትራቴጂያዊ የዕቅድ ይዘትና ተተግባሪነት ይረጋገጣል፤

17.7) **የመልማይ ኮሚቴ ግምገማ** (10%)

በተራ ቁጥር 17.6 የተዘረዘሩ ዝርዝር ነጥቦችን መነሻ በማድረግ እያንዳንዱ የመልማይ ኮሚቴ አባል ከ10% የሰጠው ነጥብ አማካይ የሚወሰድ ይሆናል፤

17.8) **የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ተወካዮች ግምገማ** (10%)

የሥርዓተ ፆታ ስብጥርን በጠበቀ መልኩ በሥራ አመራር ቦርድ የሚወከሉ ሁለት አባላት ስትራቴጂክ ዕቅድ በሚቀርብበት ጊዜ የሚገኙ ሲሆን በተራ ቁጥር 17.6 የተዘረዘሩ ዝርዝር ነጥቦችን መነሻ በማድረግ ከ10% የሰጡት ነጥብ አማካይ የሚወሰድ ይሆናል፤

**አንቀጽ 18 ታሳቢ የሚደረጉ የስርዓተ ፆታ፣ የልዩ ፍላጎት እና የአካል ጉዳተኛ ጉዳዮች፤**

18.1) የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ለሴት ተወዳዳሪዎች 5% ወይም ለአካል ጉዳተኛ ተወዳዳሪዎች 5% በአጠቃላይ ባገኙት የውድድር ድምር ውጤት ላይ ተባዝቶ ይያዝላቸዋል፡፡

18.2) አዎንታዊ ድጋፍ ከአንድ በላይ መጠቀም አይፈቀድም፡፡

18.3) አዎንታዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ተወዳዳሪዎች ከሌሎች ጋር ተወዳድረው እኩል ነጥብ ካመጡ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይመረጣሉ፡፡

18.4) አዎንታዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ወንድ አካል ጉዳተኛ እና ሴት አካል ጉዳተኛ እኩል ነጥብ ካመጡ ሴት አካል ጉዳተኛ ቅድሚያ ተሰጥቷት ትመረጣለች፡፡

18.5) አካል ጉዳተኛ የሆኑ አመልካቾች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ አመልካቾች ጋር እኩል ውጤት ቢያስመዘግቡ የቅድሚያ እድሉ ለአካል ጉዳተኛ አመልካች ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 19 የዋና ዲንና ምክትል ዲኖች አመራረጥና ምደባ፤**

የትምህርት ኮሌጆች የሥራ አመራር ቦርድ ለዲንነትና ምክትል ዲንነት ከቀረቡለት ዕጩዎች መካከል ለእያንዳንዱ ውድድር ቦታ ከ1 እስከ 3 ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ዕጩዎችን በቅደም ተከተላቸው በመለየት የቀረቡ ማስረጃዎችን፣ የውድድር ቪዲዮ እና አጠቃላይ ሪፖርት በማያያዝ ከምክረ ሀሳብ ጋር ለክልል ትምህርት ቢሮ ያቀርባል፤

**አንቀጽ 20 የክልሉ ትምህርት ቢሮ ማኔጅመንት አባላት ግምገማ (10%)**

20.1) የትምህርት ቢሮ ማኔጅመንትም የሥራ አመራር ቦርድ ያቀረባቸውን ዕጩዎች፣ ምክረ ሀሳብ እና አጠቃላይ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ ከ10% ውጤት ይሰጣል፡፡

20.2) የክልሉ ትምህርት ቢሮ ከሥራ አመራር ቦርድ የቀረበለትንና በቢሮ ማኔጅመንት የተሰጠውን ውጤት ከ100% በማጠቃለል ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበውን ተወዳዳሪ በዲንነት ወይም በምክትል ዲንነት ይመድባል፡፡

**አንቀጽ 21 ውድድሩን ስለመሰረዝ፤**

የትምህርት ሌጆች የሥራ አመራር ቦርድ በቂ ተወዳዳሪዎች አልቀረቡም ወይም የዉድድር ሂደቱ ግልጽነት ይጎድለዋል የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ ውድድሩ እንደገና እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 22 የዲኖችና ምክትል ዲኖች የአገልግሎት ዘመን፤**

22.1) የዲኖችና ምክትል ዲኖች የአገልግሎት ዘመን 5 ዓመት ነው፤

22.2) በንኡስ አንቀጽ 18.1 የተደነገገው ቢኖርም የትምህርት ኮሌጅ ዲኖችን ወይም ምክትል ዲኖችን ከተጠቀሰው ጊዜ ቀድሞ የማሟላት ሂደትን አይከለክልም፤

22.3) በንኡስ አንቀጽ 18.1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዲንነት ወይም በምክትል ዲንነት በማገልገል ላይ ያሉ በልዩ ሁኔታ የሚከለክል ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ብቻ በድጋሚ መወዳደር ይችላሉ፤

22.4) ንዑስ አንቀጽ 18.2) ድንጋጌ ቢኖርም ቢሮው ወይም የሥራ አመራር ቦርዱ የትምህርት ኮሌጅ ዲን ወይም ምክትል ዲን የሥራ አፈፃፀምና የሥነ ምግባር ጉድለት አሳይቷል ወይም ተግባሩን በተገቢው አኳኋን አልተወጣም ብሎ ካመነ፣ ያለውን ጉድለትና የአፈጻጸም ችግር በግልጽና በዝርዝር በመገምገም ከኃላፊነት ሊያነሣ ይችላል፤

**አንቀጽ 23 ቅሬታ ስለማቅረብ፤**

23.1) በውድድር ሂደት እና በማጠቃለያ ምደባ ቅሬታ ያለው እጩ ተወዳዳሪ ቅሬታውን በሁለት ቀናት ውስጥ ለመልማይ ኮሚቴ በጽሑፍ ያቀርባል፤ መልማይ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በሶስት ቀና ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡

23.2) ቅሬታ አቅራቢው በመልማይ ኮሚቴ ምላሽ ካልረካ ከመልማይ ኮሚቴ ምላሽ ካገኘበት ሁለት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሥራ አመራር ቦርድ በጽሑፍ ያቀርባል፤ የሥራ አመራር ቦርድም ቅሬታ በቀረበበት በሶስት ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡

23.3) በሥራ አመራር ቦርድ ምላሽ ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ከሥራ አመራር ቦርድ ምላሽ ካገኘበት ሁለት ቀናት ውስጥ ያቀርባል፡፡ ቢሮውም የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በሶስት ቀን ውስጥ ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በክልል ትምህርት ቢሮ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 24 መመሪያውን ስለማሻሻል፤**

የክልሉ ትምህርት ቢሮ የትምህርት ፖሊሲና የአደረጃጀት ለውጦች እንዲሁም በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ የአሰራር ተግዳሮቶች ሲያጋጥሙ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 25 ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ ህጎች፤**

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች አመራሮች ምልመላ፣ መረጣና ስምሪት ለማስተግበር የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2011 እና ተዛማጅነት ያላቸው የዘልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

**አንቀጽ 26 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ፤**

ይህ መመሪያ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ማኔጅመንት አባላት ጸድቆ በፍትሕ ቢሮ ቁጥር ተሰጥቶት ከፀደቀበት ከመጋቢት_____/2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ**

**መጋቢት 2017 ዓ.ም**

**ወራቤ**

## ተቀጽላ 1

**የትምህርት ኮሌጆች የዋና ዲን፣ የአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲን እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ውድድር ዝርዝር መመልመያ መስፈርቶች፤**

| የትምህርት ደረጃና ዝግጅት | ክብደት (15%) | የተሰጠ ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 15 | 13 | 11 | 9 | 7.5 |
| የትምህርት ደረጃ (Acadamic Rank) | 15% | 3ኛ ድግሪና ሙሉ ፕሮፌሰር ማዕረግ ያላቸው፤ | 3ኛ ድግሪና አሶሼት ማዕረግ ያላቸው፤ | 3ኛ ድግሪ ያላቸው፤ | 2ኛ ድግሪና አሶሼት ማዕረግ ያላቸው፤ | 2ኛ ድግሪ በላይ ያላቸው፤ |

| የስራ ልምድ | 15% | የተሰጠ ውጤት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 10 | 7.5 | 5 | 2.5 |
| ከትምህርትና መሰል ተልዕኮ ካሏቸው ተቋማት በትምህርት አመራርነትና በከፍተኛ ባለሙያነት የተገኘ ልምድ፤ | 10 | በትምህርት አመራርነት 10 ዓመትና በላይ ያገለገለ ወይም በከፍተኛ ባለሙያነት 15 ዓመትና በላይ ያገለገለ፤ | በትምህርት አመራርነት 7 ዓመትና በላይ ያገለገለ ወይም በከፍተኛ ባለሙያነት 11 ዓመትና በላይ ያገለገለ፤ | በትምህርት አመራርነት 5 ዓመትና በላይ ያገለገለ ወይም በከፍተኛ ባለሙያነት 8 ዓመትና በላይ ያገለገለ፤ | በትምህርት አመራርነት 3 ዓመትና በላይ ያገለገለ ወይም በከፍተኛ ባለሙያነት 6 ዓመትና በላይ ያገለገለ፤ |
| በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር፣ በምርምር ሥራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት በማስተባበር የተገኘ ልምድ፤ | 5 | በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር፣ በምርምር ሥራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት በማስተባበር 15 በላይ ያገለገለ፤ | በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር፣ በምርምር ሥራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት በማስተባበር 10 በላይ ያገለገለ፤ | በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር፣ በምርምር ሥራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት በማስተባበር 8 በላይ ያገለገለ፤ | በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር፣ በምርምር ሥራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት በማስተባበር 6 በላይ ያገለገለ፤ |
| **የጥናትና ምርምር ስራዎች** | (5%) | 5 | 4 | 3 | 2 |
| በአለም አቀፍ ወይም በሀገር አቀፍ እውቅና ባላቸው ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ስራዎች፤ | 5 | ሶስትና በላይ የታተመ የምርምር ሥራ ከቀረበ፤ | ሁለት የታተመ የምርምር ሥራ ከቀረበ፤ | አንድ የታተመ የምርምር ሥራ ከቀረበ፤ | ያልታተመ የምርምር ሥራ ከቀረበ፤ |

<table>
<tr><th colspan="22">የትምህርት ኮሌጆች የዋና ዲን፣ የአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲን እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ውድድር ዝርዝር መመልመያ መስፈርቶች፤</th></tr>
<tr><th>መልካም ስነ ምግባር</th><th>(5%)</th><th colspan="10">5</th><th colspan="10">0</th></tr>
<tr><td>ከተለያዩ ሱሶችና መጥፎ ዝንባለዎች የራቀ፣ ሚስጥር የሚጠብቅ፤ የመንግስት ሰነዶችን በአግባቡ የመጠበቅና ጥሩ የአመራር ስነ ምግባር፤</td><td>5</td><td colspan="10">ከሚሰራበት መስሪያ ቤት ጥሩ ስነ ምግባር ባለቤት ስለመሆኑ የሚገልጽ ህጋዊ የምስጋና ደብዳቤ ማስረጃ ከቀረበ፤</td><td colspan="10">ምንም ማስረጃ ካልቀረበ፤</td></tr>
<tr><th>የስልጠና ሰርተፍኬቶች</th><th>(5%)</th><th colspan="4">5</th><th colspan="4">4</th><th colspan="4">3</th><th colspan="4">2</th><th colspan="4">1</th></tr>
<tr><td>የስልጠና ሰርትፍኬቶቹ ከትምህርት አመራር፤ ከጥናትና ምርምር፤ ከዕቅድ አዘገጃጀት፤ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት፤ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፤ ተከታታይ ምዘና፤ ሰልጣኝ ተኮር ስነዘዴ ጭብጦች ዙሪያ ይሆናል፤</td><td>5</td><td colspan="4">በተጠቀሱት ጭብጦች ዙሪያ አምስትና በላይ ሰርትፍኬቶች፤</td><td colspan="4">በተጠቀሱት ጭብጦች ዙሪያ አራት ሰርትፍኬቶች፤</td><td colspan="4">በተጠቀሱት ጭብጦች ዙሪያ ሶስት ሰርትፍኬቶች፤</td><td colspan="4">በተጠቀሱት ጭብጦች ዙሪያ ሁለት ሰርትፍኬቶች፤</td><td colspan="4">በተጠቀሱት ጭብጦች ዙሪያ ሁለት ሰርትፍኬቶች፤</td></tr>
<tr><th>የስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ ይዘትና ገለፃ፤</th><th>(35%)</th><th colspan="5"></th><th colspan="5"></th><th colspan="5"></th><th colspan="5"></th></tr>
<tr><th>የስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ ይዘት፤</th><th>25%</th><th colspan="5">5</th><th colspan="5">3</th><th colspan="5">2</th><th colspan="5">1</th></tr>
<tr><td>በትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጠው ስልጠና ፍትሀዊነት፤ ጥራት፤ ተገቢነት፤ ሀገራዊና አለማቀፋዊ ግብና ስምምነት የተናበበ፤ ወቅታዊ የትምህርት ኮሌጁን ችግሮች የለየ፤ ሀገር አቀፍ የትምህርት ፖሊሲን ከግምት ውስጥ ያስገባ ግልፅ የስትራቴጂክ ዕቅድ ይዘት፤</td><td>5</td><td colspan="5">የተጠቀሱ ጭብጦች ሙሉ በሙሉ ካሟላ፤</td><td colspan="5">ከተጠቀሱ ጭብጦች አምስቱን ብቻ ካሟላ፤</td><td colspan="5">ከተጠቀሱ ጭብጦች ሶስቱን ብቻ ካሟላ፤</td><td colspan="5">ከተጠቀሱ ጭብጦች ሁለቱን ብቻ ካሟላ፤</td></tr>
</table>

| የትምህርት ኮሌጆች የዋና ዲን፣ የአካዳሚክ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ዲን እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ውድድር ዝርዝር መመልመያ መስፈርቶች፤ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የቀረቡ ስትራቴጂዎች፣ የዕቅዱ ይዘት፣ አዳዲስ ሀሳቦች መካተታቸው፤ ያልተለመደ (Innovative) ወይም (Creative) ሀሳቦች የተካተቱበት ከሆነ፤ | 5 | የእቅድ ይዘቱ አዳዲስ (Innovative) የሆኑ ሀሳቦችን ያካተተ ከሆነ እና SWOT አናልሲስ የተከተለ ከሆነ፤ | SWOT አናልሲስ የተከተለ ብቻ ከሆነ፤ | የዕቅድ ይዘት የተለመደና አዳድስ ሀሳቦችን ያላካተተ ከሆነ፤ | |
| የትምህርት ኮሌጁን ደረጃ ለማሳደግ የተቀመጡ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችና ዝርዝር ተግባራት በግልጽ የተቀመጡ ከሆኑ፤ | 5 | ኮሌጁን ወደ የልህቀት ማዕከልነት ማሸጋገር፤ | ኮሌጁን ተወዳዳሪ በማድረግ ደረጃውን ለማሻሻል የተቀመጠ ስልት ካለ፤ | ኮሌጁን ባለበት ማስቀጠል፤ | |
| የትምህርት ኮሌጁን ግንኙነት ለማሻሻልና ከተለያዩ የትምህርት ልማት አጋሮች ጋር (ዓለም አቀፋዊ፣ ሀገር አቀፋዊ፣ አካባቢያዊ) የስራ ግንኙነት በመፍጠር ተጨማሪ ሀብት ለማምጣት በግልጽ የተቀመጡ ስትራቴጂዎች፤ | 5 | በሶስቱ ደረጃ ላሉ ግንኙነቶች የታቀደ ዕቅድ ካለ፤ | በሁለቱ ደረጃ ላሉ ግንኙነቶች የታቀደ ዕቅድ ካለ፤ | በአንዱ ደረጃ ላሉ ግንኙነቶች የታቀደ ዕቅድ ካለ፤ | የተለመዱ ግኑኝነቶች ላይ ካተኮረ ወይም በመንግስት በጀት ላይ ብቻ ከተንጠለጠለ፤ |
| የመምህራንን፣ የትምህርት ኮሌጁን የአመራር እና አስተዳደር ሠራተኞችን የአመራር አቅም ለማጎልበት እና የተለያዩ (ዓለም አቀፍ፣ ሀገር አቀፍ እና አካባቢያዊ) ትምህርት ትብብሮችን ለማስፋት በግልፅ የተቀመጡ ስትራቴጂክ ዕቅድ፤ | 5 | በሶስቱ ደረጃ የመምህራንን፣ የትምህርት ኮሌጁን የአመራር እና አስተዳደር ሠራተኞችን አቅም ለማጎልበት የሚደረጉ ትብብሮችን ታሳቢ ካደረገ፤ | በሁለቱ ደረጃ የመምህራንን፣ የትምህርት ኮሌጁን የአመራር እና አስተዳደር ሠራተኞችን አቅም ለማጎልበት የሚደረጉ ትብብሮችን ታሳቢ ካደረገ፤ | በአንዱ ደረጃ የመምህራንን፣ የትምህርት ኮሌጁን የአመራር እና አስተዳደር ሠራተኞችን አቅም ለማጎልበት የሚደረጉ ትብብሮችን ታሳቢ ካደረገ፤ | |

## ተቀጽላ 2

| ለስትራቴጅክ ዕቅድ ገለፃና ቃለ መጠይቅ<br>የመልማይ ኮሚቴ አባላት ከ10% እና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ተወካዮች ግምገማ ከ10%<br>በድምሩ ከ20% ዉጤት መስጫ መስፈርት፤ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መለኪያ ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ (2%) | ከፍተኛ (1.5%) | አጥጋቢ (1%) | ዝቅተኛ (0.5%) | ምርመራ |
| 1. የሀሳብ ቅደም ተከተል በማደራጀት ገለፃውን የማቅረብ እና ለተጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ብቃት (2%) | | | | | |
| 2. የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ እና ገለፃውን በግልጽ የማቅረብና የቃላት አመራረጥ ብቃት (2%) | | | | | |
| 3. የገለፃው ይዘት ተቋሙን ከመደገፍ ወይም ከማሸጋገር (Transform) ከማድረግ አንፃር የዳበረ ሀሳብ መሆኑ (2%) | | | | | |
| 4. በገለፃው ወቅት በራስ መተማመን እና የማሳመንና ተፅዕኖ የማሳደር ብቃት እንዲሁም አቀራረቡ የማይሰለችና ሳቢ እንዲሆን የማድረግ ብቃት፤ (2%) | | | | | |
| 5. ገለፃው የትምህርት ኮሌጁን ተልዕኮ ወይም የስልጠና ጥራት እና የመማር ማስተማሩን ሂደት በማሻሻል ረገድ የሚወስዳቸውን እርምጃዎችና ስትራቴጂዎችን በግልጽ የለየ መሆኑ (2%) | | | | | |

## ተቀጽላ 3

| የክልሉ ትምህርት ቢሮ ማኔጅመንት አባላት ግምገማ ከ10% | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መለኪያ ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | አጥጋቢ | ዝቅተኛ | ምርመራ |
| | (2%) | (1.5%) | (1%) | (0.5%) | |
| 1. (2%) | | | | | |
| 2. (2%) | | | | | |
| 3. (2%) | | | | | |
| 4. (2%) | | | | | |
| 5. (2%) | | | | | |